# የዋጋ ንረትና የመንግስት ውጤታማ ክንዋኔዎች

**ዘለቀ ታሪኩ 03/24/14**

የሀገራችን ዋነኛ ጠላት ድህነት ነው፡፡ ይህ ጠላት ለዘመናት አንገታችንን አስደፍቶ የሃፍረት ሻማ እንድንከናነብ ያደረገን መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። እናም ይህን አሳፋሪ ጠላት ታግለን ካሸነፍን ሌሎች ጠላቶቻችንን በቀላሉ ድል እንደምንነሳው አያጠያይቅም፡፡ እርግጥ ድህነትን ለመቅረፍ ብሎም ለማጥፋትና የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር መንግስት ዘርፈ- ብዙ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተግባራትን አከናውኗል፤ በማከናወን ላይም ይገኛል። እነዚህ ተግባራትም ውጤታማነታቸውን በገሃድ ባስመሰከሩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች የተመሩ በመሆናቸው፤ በመላው ሀገሪቱ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት ችለዋል፡፡

በተለይም ካለፉት አራትና አምስት ዓመታት ጀምሮ፣ ለዚያውም የዓለም ኢኮኖሚና የፋይናንስ እንቅስቃሴ ችግር ላይ በነበረበት ወቅት ጭምር ኢትዮጵያ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ መቻሏን ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅትና ሌሎች ተቋማት ጭምር የመሰከሩት ሃቅ ነው፡፡ የተገኘው ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም ሁሉንም የሀገሪቱን ዜጋ በየደረጃው ተጠቃሚ ያደረገ መሆኑን ከኢትዮጵያ ህዝብ በላይ ማንም ሊመሰክር አይችልም፡፡ ለምን ቢባል የችግሩ ባለቤትም ይሁን የምፍትሔው አካል እርሱው ነውና፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ሀገርን በማሳደግ ህዝብን ከድህነት ለማላቀቅ የሚያደርገው ሰፊ ርብርብ ለደቂቃ ሳይዘናጋ ወደ ፊት እየገሰገሰ ይገኛል፡፡ እናም እያስመዘገበው ባለው ፈጣን፣ ቀጣይና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ፣ በተለይም ከዛሬ አምስት ዓመታት በፊት ተከስቶ የነበረውን የዋጋ ንረት ለመቆጣጠር የተከተለው አቅጣጫ የሀገራችን የልማት እንቅስቃሴ ሳይደናቀፍ እንዲቀጥል ያደረገ ነው። ይህ ሃቅም ልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግስት ገቢራዊ ያደረጋቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ምን ያህል ትክክለኛ መሆናቸውን የሚያረጋጥ ነው፡፡ እናም በዚህ ፅሑፍ ይህን የመንግስትን ውጤታማ የዋጋ ንረትን ቁጥጥር ርምጃን ለውድ አንባቢዎቼ ለማመላከት እሞክራለሁ። አብረን እንዝለቅ።...

መንግስት ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በገበያው ላይ የተፈጠረውን የዋጋ ንረት በሀገራችን ልማት ቀጣይነት ላይ የራሱን የሆነ ተፅዕኖ እንዳይፈጥር ፈጣን ምላሽ መስጠት መቻሉን ሁላችንም የምናስታውሰው ዕውነታ ነው፡፡ በተለይም ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ወሳኝ የልማት ትግል በመካሄድ ላይ ከሚገኝባቸው መስኮች አንዱ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነትን ለመቆጣጠር ያደረገውንና አሁንም እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ የምንዘነጋው አይደለም፡፡ በተለያዩ ጊዜያት እንደተገለፀው የተፈጠረውን የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት ለመቆጣጠር ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው ርምጃዎች ተጨባጭ ለውጥ ያሳዩ ናቸው፡፡

እናም በዚህ ፅሑፍ በሀገራችን ተከስቶ የነበረው የዋጋ ንረት በልማታችን ላይ ያስከትል የነበረውን ጫና ከመመልከታችን በፊት፣ ለዋጋ ንረት መነሻ የሆኑትን ሁለት ነጥቦች ዘርዘር አድርገን መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም የጉዳዩን መነሻ በገሃድ ሊያመላክቱን ይችላሉና። እነዚህ ሁለት ነጥቦች በሀገር ውስጥ መነሻን መሰረት ያደረጉ የምርት እጥረትና የዋጋ ጭማሪ እንዲሁም ከሀገር ውጭ የሚገቡ የተለያዩ ዕቃዎች የሚያሳድሩት ያልተመጣጠነ የገበያ ዋጋ ናቸው፡፡

እንደሚታወቀው ሀገራችን በተመረጠ ሁኔታ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ባለበት የነጻ ገበያ ሥርዓት መመራት ከጀመረች የሁለት አስርት ዓመታት ዕድሜን አስቆጥራለች፡፡ ይህም በሀገር ውስጥ ፈጣን፣ ዘላቂ፣ ተወዳዳሪና ከተጽዕኖ የፀዳ የንግድ ሥርዓት እንዲሰፍን ያስቻለ ነው፡፡ የገበያ ስርዓቱ ሸማቹም ሆነ አምራቹ ያለምንም ጣልቃ ገብነት የንግድ ልውውጡን እንዲያካሂድ ሙሉ ነጻነት የሰጠ ከመሆኑም ባሻገር፤ ልማታዊ ባለሀብት በጥራትና በብዛት እንዲፈጠርም የማይተካ ሚና ተጫውቷል፤ በመጫወት ላይም ይገኛል፡፡

እርግጥ መንግስት የነፃ ገበያ ሥርዓቱን ከመዘርጋት ጀምሮ ስር እንዲሰድ በማድረግ በኩል የአንበሳውን ድርሻ ይዞ ችግሩን በቁርጠኝነት እየተወጣ ይገኛል፡፡ ያም ሆነ ይህ እስቲ ለተከሰተው የዋጋ ንረት ዋነኛ መንስዔ የሆነውን ከሀገር ውስጥ ከሚመነጩ ምርቶችና የገበያ አለመረጋጋትን ጉዳይን በቅድሚያ እንመልከት፡፡ ለዋጋ ንረትና ለኑሮ ውድነት ምክንያት ሊሆኑ ችለው ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ ሀገራዊ መሰረት የነበራቸው ምርቶች ላይ ተንተርሶ የተፈጠረው የገበያ ዋጋ መናር ክስተት ነበር፡፡ በተለይም ከአምስት ዓመታት በፊት የሀገራችን የግብርና ምርቶች በከፍተኛ መጠን እያደጉ በነበሩበት ወቅት በከተሞች ውስጥ ምርቶች ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ አሳይተው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ከኢኮኖሚው ዕድገት ጋር ተያይዞ የተከሰተ ነበር፡፡ አዎ! የህብረተሰቡ ገቢ

እየጨመረ በሄደ ቁጥር ለመሰረታዊ ሸቀጦች ያለው ፍላጎት አብሮ ሊጨምር መቻሉ ነባራዊ ዕውነት ነው። የግብርና ምርት አቅርቦት በእጅጉ አድጎ በነበረበት በዚያ ወቅት የሸቀጦች ፍላጎት አብሮ በማደጉ ምክንያት ዋጋው ከተገመተው በላይ በላቀ ደረጃና ፍጥነት ሊጨምር ችሏል፡፡

እርግጥም ባለፉት ዓመታት ለታየው የዋጋ ንረት አንዱ ምንጭ የእህል ዋጋ ያለማቋረጥ መጨመር ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ የተፈጠረው ለገበያው የሚቀርበው ትርፍ ምርት ኢኮኖሚው በሚፈልገው ልክ አለማደጉን ተከትሎ እንዲሁም የገበያው ተዋንያን የእህል ዋጋ እንዲጨምር ለማድረግና ይጨምራል ከሚለው ግምት በመነሳት የሚያቀርቡትን መጠን መቀነሳቸው ብሎም ዋጋውን በቀጣይነት በመጨመራቸው ነው፡፡ ተግባሩ ከአርሶ አደሩ ጀምሮ እስከ ነጋዴው ድረስ ባሉ ተዋንያን አማካኝነት የተፈጸመ ሲሆን፣ የግብይት ሥርዓቱ ቅልጥፍና የጎደለውና ለውድድር በበቂ መጠን ያልተረጋጋጠ መሆኑን የሚያሳይ ጭምርም ነበር፡፡ የገበያ ሥርዓቱ ለሀገራችን አዲስ እንደመሆኑ መጠን፣ ለዋጋ ንረቱ የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ አንድን ምርት ከአምራቹ ወደ ተጠቃሚው ለማድረስ በርካታ የግብይት ሰንሰለቶችን ማለፉ የግድ በመሆኑ፣ እነዚህ ሰንሰለቶች በየምዕራፉ ተገቢ ያልሆነ ወጪን ማስከተላቸውና ይህም በሸቀጦች የመሸጫ ዋጋ ላይ የሚንጸባረቅበት ሁኔታ እንዲከሰት አድርጓል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም። የምርት መጠን ማነስም ሌላኛው የዋጋ ንረቱ ምክንያት ነበር፡፡ ወደ ገበያ የሚወጣው የምርት መጠን ከህብረተሰቡ ፍላጎት አኳያ ያነሰ መሆኑ የእህል ዋጋው ጭማሪ እንዲያሳይ ማድረጉ አይታበይም፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም የህብረተሰቡን የዕድገት መጠን ተከትሎ የመግዛት አቅም በእጅጉ እያደገ በመምጣቱ ቀደም ሲል ከነበረው ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም፡፡ ቀልጣፋ የገበያ ሥርዓት ያለመኖርም ለዋጋ ንረቱ መባባስ የራሱን አሉታዊ ሚና ተጫውቷል። የባንኮች የፋይናንስ ሥርዓት ቀልጣፋ ያለመሆን ሁኔታም እንዲሁ፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የዋጋ ንረት ሳቢያ ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎች ዋጋ መጨመር ነው። እናም እነዚህ ሀገራችን ውስጥ የማይገኙና ከውጭ ብቻ የሚመጡት ምርቶች በዶላር የሚገቡ በመሆናቸው በግብይይት ስርዓታችን ላይ የራሳቸውን ተደማሪ ጫና ለመፍጠር ችለዋል።…እንግዲህ እዚህ ላይ 'እነዚህን ሁለት መሰረታዊ የዋጋ

ንረት መንስኤዎችን መንግስት እንዴት ሊቆጣጠራቸው ቻለ?' የሚል ጥያቄ ማንሳት የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው በልማት መፍጠን ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ የፍላጎቶችም ሆኑ የዋጋ ጭማሪዎች ሊገቱ የሚችሉት በዘላቂነት ልማቱን በማፋጠን ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ይህን ሃቅ በጥልቀት ተገንዝቦ ለተፈጠረው የገበያ አለመረጋጋት ዘላቂ መፍትሄ ሊሰጡ የሚችሉ የልማት ስራዎችን አከናውኗል፣ በማከናወን ላይም ይገኛል፡፡ ለአብነት ያህልም በሀገራችን ተከስቶ የነበረውን የስኳር እጥረት ለማቃለል አስር የስኳር ፋብሪካዎች በፍጥነት እየገነባ መሆኑን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ አዳዲስ ስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ በተጨማሪ የስኳርን ችግር በአስተማማኝ ሁኔታ ለመቅረፍ የሚያስችሉ ተግባራትን በነባር የስኳር ፋብሪካዎች ውስጥ በእጥፍ የማስፋፋት ፕሮጀክቶችን በመዘርጋት ለውጤት በቅቷል፡፡

በሌላ በኩልም መንግስት ዳግም ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የገበያው ሁኔታ የተረጋጋና የተሳለጠ እንዲሆን ያደረገው ጥረት የተሳካ ውጤት አስገኝቷል፡፡ እርግጥ ባለፉት አምስት ዓመታት የሀገሪቱ የዋጋ ንረት በከፍተኛ ደረጃ ላይ መወጣቱን ተከትሎ፣ መንግስት ከላይ የጠቀስናቸውን ርምጃዎች በመውሰድ ችግሩን በአጭር ጊዜ ለመፍታት መቻሉ የተመለከትነው ሃቅ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ ሊሆን የሚችለው ደግሞ መንግስት በ2003 ዓ.ም የነደፈው የአምስት ዓመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር በሚያስችል ሁኔታ የተቀየሰ መሆኑ ነው፡፡

አዎ! በልማት ዕቅዱ ላይ የተካተተው ምርትን በእጥፍ የማሳደጉ ስትራቴጂ የዋጋ ንረቱን በመቆጣጠር የላቀ አስተዋጽኦ አበርክቷል፣ እያበረከተም ነው፡፡ የዕቅዱን የሶስት ዓመታት አፈጻጸም ስንመለከት የዋጋ ንረቱን በመቆጣጠር ረገድ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ በተጨባጭ ከአምስት ዓመት በፊት ተከስቶ የነበረውን የዋጋ ንረት ከአሁኑ ጋር ሲነጻፀር ልዩነቱ በእጅጉ እንደጠበበ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

እንደሚታወቀው በ2003 ዓ.ም ከግብርናው የተገኘው አጠቃላይ ምርት ሁለት መቶ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት በተከተለው ስትራቴጂ የግብርናው መስክ ውጤታማነት ከ2002 ዓ.ም ጋር ሲነጻጸር በላቀ ሁኔታ እንዲጨምር አድርጎ ነበር፡፡ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም የዋጋ ንረት ለማስተካከል ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተገንዝቦ

ተግባራዊ እርምጃ ሲወሰድ ቆይቷል፡፡ በዚህም አርሶ አደሩ በ2005 የምርት ዘመን የተሻለ ምርት እንዲሰበሰብ የተለያዩ ድጋፎችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም በ2005 ዓ.ም የምርት መጠን የተሻለ እንዲሆን አስችሏል፡፡ በያዝነው 2006 ዓመተ-ምህረትም የምርቱ መጠን ካለፈው ዓመት የተሻለ እንደሚሆንና የዋጋ ንረቱም ይበልጥ የሚስተካከልበት ሁኔታ መፈጠሩ አይቀሬ ነው፡፡ ታዲያ ለምርት መጠኑ ማደግ መንግስት ከፍተኛ ተግባራት ፈፅሟል–አርሶ አደሩ ምርጥ ዘርን፣ ማዳበሪያንና ሌሎች አቅርቦቶችን በበቂ ሁኔታ አግኝቶ ወደ ምርት ተግባር እንዲገባ በማድረግ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ለአርሶ አደሩ ልዩ ልዩ የቴክኒክ ድጋፎችን የመስጠት ስራዎችን በመከወን ውጤታማ ተግባራትን በመፈፀሙ የዋጋ ንረቱ ይበልጥ እንዳይንር ለመቆጣጠር ችሏል፡፡ ሌላው የባንኮች የፋይናንስ ሥርዓት የማስተካከል ሁኔታና የዜጎች የቁጠባ አቅም እንዲያሳድጉ በመደረጉ ሳቢያ የዋጋ ንረቱን ለማርገብ የተቻለበት ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም የብድር ሥርዓቱን የመቆጣጠር ተግባር በገበያው ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ መረጨቱ የዋጋ ንረት እንዲስተካከል የሚያደርገው የቁጥጥር ዘዴ የመፍትሄው አንዱ አካል አድርጎ በመንቀሳቀሱ ስኬታማ ሆኗል፡፡

ባለፉት ዓመታት የኢኮኖሚው የማምረት አቅም የተሻሻለ፣ ቀጣይና ተከታታይነት ያለው እንደነበር አይካድም፡፡ በርግጥ ይህ ልዩነት እምብዛም የገነነ ነው ብሎ መጥቀስ ግን አይቻልም፡፡ ይህ ሁኔታ በማክሮ ኢኮኖሚው ላይ ጫና እንዳይፈጥር መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ የዋጋ ንረቱን ሊቆጣጠረው እንደቻለ መገንዘብ እንችላለን፡፡

ሌላኛው በሀገራችን ለተከሰተውን የዋጋ ንረት መነሻ የሆነው ከዓለም የገበያ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የመጣው ጭማሪ መሆኑን መንግስት በወቅቱ ተጨባጭ እማኞችን በመጥቀስ በዝርዝር ለማስረዳት የቻለበት ሁኔታ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ እርግጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈጣንና ሰፊ የሆነ የገበያ ትስስር የተፈጠረበት የግሎባላይዜሽን ወቅት ላይ የምንገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ታዲያ ይህን ትስስር ስንመለከት በኢኮኖሚው የበለጸጉትን ብቻ ሳይሆን፣ በማደግ ላይ የሚገኙትን ብዙሃኑን የዓለም ሀገራት ያካትታል፡፡ ሀገራችንም ከዚሁ ትስስር ወጥታ ለብቻዋ ልትኖር አትችልም። በግሎባላይዜሽን ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን በመከላከልና የትስስሩ አካል በመሆን የተጠናከረ ተግባራትን በማከናወን ላይ ትገኛለች፡፡

በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ የሚታዩ አማኝ ማስረጃዎች እንዲያመለክቱት፤ ሀገራችን ከመቶ ሃያ በላይ ከሆኑ ሀገራት ጋር የንግድ ልውውጥ በማድረግ ላይ ናት፡፡ በገበያውም እንደ ቡና፣ የቅባት እህሎችና ሌሎች ለዓለም አቀፍ ገበያ የሚሆኑ ሀገራዊ ምርቶችን በመሸጥ ጠቀም ያለ የውጭ ምንዛሪ እያገኘች ሲሆን፤ በምትኩም እንደ ነዳጅ፣ ብረት፣ ማዳበሪያ…ወዘተ. ምርቶችን ታስገባለች፡፡ ታዲያ ይህ የገቢና ወጪ የሀገሪቱ እንቅስቃሴ እየተከናወኑ ላሉት የልማት ስራዎች ወሳኝ ድርሻ እንዳላቸው መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሆኖም እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ነገር፤ ሀገራችን ከውጪ የምታስገባቸው ምርቶች ለኢኮኖሚ ዕድገትዋ ትልቅ ፋይዳ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን በዓለም ገበያ ላይ የተፈጠረውን የዋጋ ጭማሪ ተከትሎ ሀገራችን ከውጭ የምታስገባቸው እንደ ነዳጅና ሌሎች የምርት ዓይነቶች ላይ የዋጋ ጭማሪ መፈጠሩ ከዚሁ ምክንያት የመነጨ መሆኑን መረዳት ተገቢ ይመስለኛል፡፡

በርግጥ በወቅቱ በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ የአንድ አንድ ምርቶች ዋጋ መናር ትልቅ መንስዔ ከዓለም አቀፍ የገበያ ሁኔታ ጋር ሊያያዝ የሚችል ቢሆንም፤ ለችግሩ ሌሎች ተጨማሪ መንስኤዎች ነበሩ፡፡ ቀደም ብዬ የገለጽኳቸውና በሀገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች እየተፋጠኑ ከሚገኙ የልማት ስራዎች ጋር በተያያዘ የአንድ የምርት ዓይነት ተፈላጊነት መጨመሩ ለዋጋ ንረቱ መናር ምክንያት መሆኑ አይታበይም፡፡

ለነገሩ ይህ በልማቱ ምክንያት የሚፈጠር የዋጋ ጭማሪ የማይገመትና እንደ ከባድ ችግር የሚቆጠር አይደለም፡፡ ልማት እስካለ ድረስ የአንዳንድ ምርቶች አስፈላጊነት መጨመሩ አይቀሬ ነው፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስም አምራቹ በእነዚህ የምርት ዓይነቶች ላይ ምክንያታዊ የሆነ ጭማሪ ሊያደርግባቸው የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ለምን ቢባል፤ ከንዋኔው የነፃ ገበያ ሥርዓቱን የሚጻረር ባለመሆኑ ነው፡፡ በወቅቱም እንደ ሲሚንቶ፣ ብረታ ብረት፣ የቅባትና የአንዳንድ የጥራጥሬ እህሎች ላይ የታየው ጭማሪም ከዚሁ አኳያ በማሳያነት ሊቀርብ የሚችል ስለሆነ ነው፡፡

ከውጭ የምናስመጣቸው ምርቶች የዶላር ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ መጨመሩም ለዋጋ ንረቱ አንዱ መንስኤ ነበር፡፡ ይህም በወቅቱ የዓለም የነዳጅና የማዳበሪያ ዋጋ ሽቅብ ከመውጣቱ ጋር ተያይዞ፣ ከውጭ ወደ ሀገራችን ይገቡ በነበሩ ምርቶች ላይ የዋጋ ጭማሪውን አባብሷል ማለት ይቻላል፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን ነገር፤ የዓለምን ገበያ መቆጣጠር

ስለማይቻል ይህንን ችግር ከምንጬ ማድረቅ የማይችልበት ሁኔታ መኖሩ ነው። ከዚህ በተጨማሪም ከውጭ የምናስገባቸው ምርቶች የዶላር ዋጋ ባይጨምርም፤ የብር ተመን በመቀነሱ ምክንያት ዋጋቸው ጨምሮ የዋጋ ንረቱ ማስከተሉ አልቀረም፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን በዓለም ገበያ አማካኝነት በወቅቱ በሀገራችን የተከሰተውን የዋጋ ንረት ለመቀነስ ብሎም አደጋውን ለመቅረፍ ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም፡፡ ነዳጅን ጨምሮ ሌሎች ከውጭ የሚገቡ የተወሰኑ የምርት ዓይነቶች ላይ ጭማሪው ተስተውሏል፡፡ ጭማሪው በቂ ምክንያት ያለው በመሆኑ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሁኔታውን ለመቀበል አልተቸገረም ነበር፡፡ ግና መንግስት በዓለም አቀፍ ገበያ መታወክም ሆነ በልማቱ ምክንያት የተፈጠሩት ጊዜያዊ ተጽዕኖዎች ህዝቡን የሚጎዱ አይደሉም ብሎ እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም፡፡ እናም የነጻ ገበያ ሥርዓቱን የማያስተጓጉሉ ፈጣን ውሳኔዎችን መውሰድ ችሏል፡፡

በወቅቱ በነዳጅና በግንባታ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የተፈጠረውን የገበያ አለመረጋጋት በማስተካከል መንግስት ከካዝናው በመደጎም ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ከማድረጉም በተጨማሪ፤ አንዳንድ ምርቶችም ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ የፈቀደበት ሁኔታ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡ እርግጥ የገበያ ሁኔታውን ለማረጋጋት ሲል ከራሱ ካዝና መደጎሙም ይሁን ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ በበጀቱና ገቢው ላይ ቀላል የማይባል ተፅዕኖ እንዳለው አያጠያይቅም፡፡ ሆኖም እነዚህን ተፅዕኖዎች እንዳሉ እየተገነዘበም ቢሆን፣ ተገቢ ርምጃዎችን ከመውሰድ ወደ ኋላ አላለም ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የመንግስት ሩቅ አሳቢነትን አጉልቶ የሚያሳይ ሃቅ ነው፡፡

መንግስት የዋጋ ንረቱን በማስተካከል የተለያዩ እርምጃዎች በመውሰድ የሀገራችን የልማት እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረጉን በተጨባጭ ለመመልከት ችለናል፡፡ በአሁኑ ወቅት እየወሰዳቸው ካሉ ርምጃዎች መካከል የብድር ሥርዓቱን መቆጣጠር መቻሉ ተጠቃሽ ሲሆን፤ ሌላው ከነጻ ገበያ ሥርዓቱ ጋር ተያይዞ በገበያው ውስጥ የተሰራጨውን ከፍተኛ መጠን ያለው የብር ተመን ንረት እንዳይፈጠር ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ ሌሎች ማሳያዎች ናቸው፡፡

ለዋጋ ንረቱ መባባስ ምክንያት ሆነው የቆዮት ከላይ የጠቀስናቸው ጉዳዮች ብቻ አይደሉም። ከንግዱ ማህበረሰብ ውስጥ የራሳቸውን ፍላጎት ለማርካት ብቻ በዋጋ

በመመሳጠር ክፍተት ሲፈጥሩ የቆዩበት ስግብግብ ነጋዴዎች የአሰራር ሁኔታም አንዱ ነበር። ይህ አሰራር ለሀገርና ለህዝብ ምንም ሊፈይድ እንደማይችል መንግስት በሰጠው በቂ የአቅም ግንባታ ተግባር ሊስተካከል ችሏል፡፡ በቀጣይም መንግስት የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር እንዲሁም የዜጎችን የማምረት አቅም ለማጠናከር ገቢያቸውን የማሳደግ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳት የመቋቋም ብቃት እንዲያዳብሩ የተጠናከረ ስራ መተግበሩን እንደሚቀጥል ቀደም ሲል ካከናወናቸው አመርቂ ክንዋኔዎች ለመረዳት አይከብድም ፡፡

ቀደም ሲል በማሳያነት የጠቀስኳቸው መንግስታዊ ተግባሮች፣ ህዝቡ በዋጋ ንረቱ ከፍተኛ ጉዳት እንዳይደርስበት ትልቅ ዕገዛ እንዳደረጉ ቢታመንም፤ ሙሉ ለሙሉ ተወግደዋል ማለት እንዳልሆነ ግን ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም፡፡ እናም የዋጋ ንረቱን ቀጣይነትና ዘላቂነት ባለው መንገድ ለማስወገድ ከፍተኛ ድርሻ በሚኖራቸው የምርት ዓይነቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ ርብርቡን አጠናክሮ መቀጠል የሚገባ መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ ማንም የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው፤ በፈጣን ልማት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ የፍላቶችንም ሆነ የዋጋ ጭማሪዎች ለማስወገድ ዋናውና ዘላቂው መፍትሔ ልማቱን ማፋጠን ብቻ ነው፡፡

በጥቅሉ በሀገራችን ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ የተከሰተው የዋጋ ንረት በድህነት ተኮር ቅነሳ ስራዎች ላይ የጎላ ተጽዕኖ ሳይፈጥር በሂደት ለመቆጣጠር መንግስት ያከናወነው የተቀናጀ ዘርፈ ብዙ ርምጃዎች ይበል የሚያሰኙ ናቸው፡፡ ይህም የሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስር እየሰደደ በሄደ ቁጥር፤ ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ አሉታዊ ክስተቶችን የመቋቋም ብቃቱ ከፍተኛ ሊሆን እነደሚችል፤ የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር የተወሰዱት ርምጃዎች አመላካች መሆናቸውን ለመገንዘብ የሚያዳግት አይመስለኝም፡፡ በመሆኑም የልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግስት የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር የወሰዳቸው ውጤታማ ርምጃዎች ስርዓቱ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን ራስ በራሱ እያረመ ብሎም እየፈታ የሚሄድ መሆኑን ያስመሰከረበት ተግባራት በመሆናቸው ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል። ነገ እነ ኮሪያና ታይዋን የረገጡትን ድንጋይ መርገጣችን አይቀሬ መሆኑን መተማመኛ ያለን መሆናችንም ጭምር። አበቃሁ።